# ብሆንማ ኖሮ

ስናየው የኖርነው ከጥንት ጀምሮ፤
ሲታገል ሲያታግል ትግሉን አጠናክሮ፣
ፋሺዝም ተዋግቶ ቅራኔን ወጥሮ
አለ ኢሕአፓ ከሕዝብ ጋር አብሮ

የአገሬን አርበኛ ብሆንማ ኖሮ
እጋደል ነበረ አንቄ ጉሮሮ
እለቅመው ነበረ ያን የሰው ዝንጀሮ
እዘረጋው ነበር ቀንጥሼ እንደ ዶሮ

የኢሕአፓ ታጋይ ብሆንማ ኖሮ
አነጥፈው ነበር መትቼ በመሮ
አይኖራትም ነበር ሲደልቅ ከበሮ
አይቀልድም ነበር ኢትዮጵያን ወሮ
ይፈነዳ ነበር በድኑ ተወጥሮ

ብሆንማ ኖሮ ታላቁን አባይ
እጠርገው ነበረ ጦብያን ገዳይ
አቀልጠው ነበረ እንደ አፋር ፀሐይ
አገርና ሕዝብን ወገን ከፋፋይ

ስናየው የኖርነው ከጥንት ጀምሮ

ሲታገል ሲያታግል ትግሉን አጠናክሮ

ፋሺዝም ተዋግቶ ቅራኔን ወጥሮ

አለ ኢሕአፓ ከሕዝብ ጋር አብሮ

ሆኜ ብገኝማ የኢሕአወሊ ታጋይ

አቦይ ስብሐትን የደደቢት ድንጋይ

የሚከደምለት ያን የትግሬ ጠንቋይ

የወየነ ሽፍታ ቀዬ አፈናቃይ

እደፋው ነበረ ደጎል አደባባይ

እንጨቱን አርዝሜ ገመዱንም ከላይ

እሰቅለው ነበረ ያንን አባይ ፀሐይ

ሆኜ ብገኝማ ጀግና ወታደር

ወገኑን ጠባቂ አስከባሪ አገር

ደሙን አፍሳሽ ዜጋ ክብር ለአገር

ዝም አልልም ነበር አገር ሲመተር

ለሱዳን ሲለገስ የጦብያ ምድር

አስቀዝነው ነበር በፍርሐት ሽብር

የቋራን መተማ አስበልቼ አፈር

ቆሜ እስቅ ነበር መሬት ሲቀበር

ስናየው የኖርነው ከጥንት ጀምሮ

ሲታገል ሲያታግል ትግሉን አጠናክሮ

ፋሺዝም ተዋግቶ ቅራኔን ወጥሮ

አለ ኢሕአፓ ከሕዝብ ጋር አብሮ

ስኳድ አባልማ ብሆንማ ኖሮ

እደፋው ነበረ ቤተመንግሥት ጓሮ

አባርረው ነበረ ደደቢት ሽራሮ

አይኖራትም ነበር አዲስ ላይ ዘንድሮ

ፀሐዬና ስብሐት አዲሱ በረከት

ግልገል ቡቹሎቹ የክልል ነገስታት

በመትረየስ ገዳይ ህጻናት አዛውንት

ያንሳቸዋል ታድያ ሞትና ስቅላት?

ይታወስ ይወደስ ገሞራው ዮሐንስ

ቅኔን የሚዘርፈው በሥጋና በነፍስ

ይወለድ ደጋግሞ እስጢፋኖስ አዲስ

እንዲያጽናናን ዳግም ትግላችን ሲታደስ

ስናየው የኖርነው ከጥንት ጀምሮ

ሲታገል ሲያታግል ትግሉን አጠናክሮ

ፋሺዝም ተዋግቶ ቅራኔን ወጥሮ

አለ ኢሕአፓ ከሕዝብ ጋር አብሮ